ወ ቅ ደ ለ

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) ልሣን

የዐማራ ኅልውና መጠበቅ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!

ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!

ቅጽ: ፩ ቁጥር: ፫ ቀን: ታህሳስ ፫ ፪ሺ፲

በየ15ቱ ቀን ዘወትር ኀሙስ የሚወጣ



## የትግሬ ወያኔ ወደ እውነተኛ ቁመናው ሲመለስ!

የግለስብ ሁለንተናዊ ቁመናው የሚገለጥ ከሚመጣበት መህበረሰብ አኳያ ነው። ግለስቦቹ ተቧድነው የሚፈጥሩትም ማህበርና ድርጂትም ላይ የዚያው ማህበረሰብ አሻራ አብሯቸው ይኖራል። ለምሳሌ በአፍሪካ ቀንድ ያሉ ማህበረሰቦችን በዚህ አኳያ መዳሰስ ይቻላል። ይህን ማህበራዊ እይታ ያፍሪካ ቀንድ ወስጥ የሰፈሩ የተለያዩ ማህበረሰቦች የሚጋሩት ቢሆንም በሱማሌ፣ በኤርትራና በትግሬ ማህበረሰቦች መሀል ባያሌው የሚታየው በቤተሰባዊ (ክላን) አመለካከት ዙሪያ የሚታይ ማህበረሰባዊ መከፋፈል የላቀ ነው።

በዚህ ረገድ ዛሬ ለነጻዪቱ ሱማሌ መበታትን ከፍተኛውን ሚና የተጫወተ የህዝቧ በክላን ዙሪያ ያጠነጠነ አመለካከት በማደግ ላይ የነበረውን ሀገራዊ አመለካከት ስለደፈጠጠው ነው። ዚያድ ባሬ የኦክቶበር አብዮት ብሎ የሰየመውን የ1962ዓም የመፈንቅ ለመንግስት ሲመሰርት ዋና የአገዛዙ መመሪያ አድርጎ ያስቀመጠው የሱማሊያን አምስት የተለያዩ ግዛቶችን በአንድ የተጠቃለለች ታላቅ ሱማሌ ስር የማምጣትን ህልም ነበር። ዚያድ ባሬ ይህንን መመሪያ ዋናው የአገዛዙ ርእዮት ሲያደርግ ኢላማው የማህበረሰቡ ዋና ድክመት የሆነውን የቤተሰባዊ(የክላን) አመለካከትን በአንድ ሱማሊያ ተብላ በምትጠራ አዲስ ሀገር ዙሪያ ለማሰለፍ ነበር። እንዳለውም ፊደል ላልነበረው ቋንቋ የላቲን ፊደልን እንዲይዝ አደረገ። የሀገሪቱን የአስተዳደር አይነት ሶሻሊዝም ነው ብሎ አወጀ። ሀገራዊ ታላቅነቱን እውን የሚያደርግለት ጦሩን ገነባ።

## የትግሬ ወያኔ ወደ እውነተኛ ቁመናው ሲመለስ!

ከፍተኛ የሆነ ብሄረተኝነትን የሚቀሰቅስና በአንድ የጋራ ጠላት ዙሪያ የሚያስቆም ጠላት ተመረጠለት። ኢትዮጵያ ዋና የጋራ የተለያዩትን አስተባባሪ የምትሆን ተደርጋ የሱማሌ ብሄራዊ ጠላት ሁና ተመረጠች።

የዚያድ ባሬ የማህበረሰብ ችግርን በጋራ ሰው ሰራሽ ጠላት ዙሪያ እንዲቆም የማድረግ አባዜ በጸሓይ እንደተመታ ጤዛ የረገፈው በኢትዮጳያ ላይ በወሰደው ወራራ ላይ ሆነ። ሱማሌ በወረራው በደረሰባት ሽንፈት ወደነበረችበት ቁመናዋ እንድትሸበሸብ ተደረገች። የህብረተሰቧ ቁመና በአሸዋ ላይ ከተገነባው የታላቋ ሱማሌ፣ ከሰው ሰራሽነት ወደእውነቱ የክላን ዓለም ስሪቷ እንድትመለስ ሆነ። መሀሉ ዳር ሆነ። ሁሉም ወደጎጆው ተመልሶ ከፍርስራሹ የቻለውን ለማንሳት የራሱን ጦር አቁሞ ይፋለም ገባ ። እናም ሱማሌ ፈረሰች።

ይህ ክስተት ባጋጣሚ የመጣ ሳይሆን መሆን የነበረበት ነው የሆነ፡፡ የኤርትራንም አፈጣጠር በትይዩ ማስቀመጥ ይቻላል። የኤርትራን አንድ ሀገርነት እውን ለማድረግ እንደ ዲናሚት ፈንድቶ እንዳልነበር ሊያደርግ የሚችለውን የአውራጃ ፖለቲካን አርግቦ አዲስ ሀገር ለመመስረት የተደረገው ትግል የአዲሲቱ ሀገር ዋና መገለጫ ታሪክ ነው ማለት ይቻላል። እንደ ሱማሊያው የክላን ታሪክ ሁሉ የኤርትራውን የአውራጃ ፖለቲካን ለማዳፈንና አንድ አመለካከት ለመፍጠር የተሄደበት መንገድ አንድ የጋራ ጠላት ኢትዮጵያን መፍጠር አስፈላጊ ነበር። በዚህ ጎዳና ውስጥ ሲጓዙ ደም ያራጨ የርስ በርስ ጦርነቶችንም አስተናግደዋል። ከኤርትራ እንደሀገር መቆም በኋላም ባለው የሸአብያ አገዛዝ ስር እንደገና ተመልሶ ያቆጠቆጠና ለእንደገና መፍረሷ ምክንያት ስለመሆኑ የሚነገርለት የአውራጃዊ ፖለቲካ ነው። ይህ በሚገባ በፕሮፌሰር ተስፋጽዮን መድህኔ "ኤርትራ እንደናት ሀገር፣ ችግሮችና ፈተናዎች ትናንትም ዛሬም"" በሚል በ2013 የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ ላይ በሚገባ የተነገረ ጉዳይ ነው፡፡

የዛሬው የወያኔ ሐርነት ትግራይ ከትግራዊ ወደ አድዋዊነት ተፈጥሮው የመመለስ ክስተት መሆን የነበረበት ነው። እዚህ አሁን የምንመለከተው ሁኔታ ውስጥ ከመመለሱ በፊት ህወሀት ሲመሰረት ይህ አውራጃዊነት የድክመቱ መሰረት እንደነበር የተገነዘበ ድርጅት ነበር። በመሆኑም እንደ ህብረተሰብ የነበሩ ድክመቶቹን ለመሸፈን በሚል የሚከተሉትን ሁለት ድክመቶችን ለይቶ ነበር።

እነሱም፣

1 የተነሳበት ያውራጃዊ የፖለቲካ ታሪክ የቤት አድዋ፣ የቤት ተምቤን፣ የቤት ሽሬ፣ የቤት እንደርታ፣ የቤት አጋሜ በሚል ተከፋፍሎ የቆየ መሆኑ የድክመት መገለጫው መሆኑን ተረድቶ ነበር። ይህንን ድክመቱን ለመሸፈን የሄደበት መንገድ አመራሩን በተቻለ መጠን ከሁሉም አውራጃ የሚወከሉበት እንዲሆን ማድረግ ነበር።

# የትግሬ ወያኔ ወደ እውነተኛ ቁመናው ሲመለስ!

2 የትግሬው ድርጂት ለተነሳለት ዓላማው አንድ ሁኖ መድረስ አንድ የሚያደርገው የጋራ ጠላት አማራን መፍጠር ነበረበት። እናም አደረገ። ሌላው ከዚሁ የጸረ አማራ ትንግርቱ ጋር በመያያዝ ካናሳ ማህበረሰብ የመምጣት ችግሩን ለመሸፈን አንድ ትልቅ የጸረ አማራ ግንባርን በሀገር አቀፍ ደረጃ ማዋቀር ዋናው ስራው ነበር። ህወሀት ይህንን ሲያደርግ ድከመቱ አውራጃዊ አመለካከት ብቻም ሳይሆን የኢትዮጵያን ማእከላዊ መስተዳድርን ለማፍረስና በቁጥጥሩ ስር ለማምጣት ከተነሳበት አናሳ ማህበረሰብ አቅም ውጪ መሆኑን የተገነዘበ በመሆኑ የጸረ ኢትዮጵያ ሀይሎችን ያካተተና በሱ አመራር ሰጪነት ግንባር ስር የሚቆም ሀይል መፍጠር ሌላው እስትራተጂክ ግቡ ነበር። ይህንንም አደረገ።

ይህ ከዚህ በላይ የተመለከትነው ባጭሩ የሚያሳየው በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ያሉ ካናሳ የክላንንና የአውራጃ አመለካከት ዘንድ የመጡ አፍራሽ የፖለቲካ ሀይሎች የተጫወቱትን የሰው ሰራሽ የጠላት ፍለጋ ፖለቲካን ነው:: ለእነዚህ ሀይሎች በጋራ ጠላትነት የተመረጡት ኢትዮጵያና አማራ መሆናቸውም ባጋጣሚ አልነበረም። ሁሉም ይዘው የተነሱት በባንዳነት ቁመው የታገሉለትን የወራሪውን የጥልያንን የጸረ ኢትዮጵያ አስተምህሮን ነበር። ዛሬ በሱማሌ ያየነውና ነግ በኤርትራና በትግሬ የምናየው እንደአመጣጣቸው ሁሉ መመለሻቸውም ተመሳሳይ መንገድ መሆኑን ነው። ውደነበሩበት የመመለስና የመበታተን ጎዳና ውስጥ የመግባት። ዛሬ ህወሀት ባለፉት 27 ዓመታት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በተለይም በአማራው ህዝብ ላይ ያደረሰው የዘር እልቂት ድርጊት የሰውን ልጅ እንደ ህዝብ በማጥፋት የሚያስጠይቀው ወንጀል ***ነው። ዛሬ በየትኛውም የዓለም ህዝብ ውስጥ የህገ-መንግስት ከለላ የሌለው፣ ብቻውን ለኢላማ ተነጥሎ የተቀመጠ ህዝብ የአማራ ህዝብ ብቻ ነው።*** በመሆኑም ማንም ተነስቶ በዚህ ህዝብ ላይ ኢሰባዊ እርምጃ በመውሰዱ የሚጠይቀው የለም። ለደረሰበትም እልቂት የተጠየቀ ግለሰብም ሆነ ድርጂት የለም ። ወደፊትም አይኖርም። ለዚህም ነው ለአማራው የቀረ የመጨረሻ ምርጫው እራሱን አደራጅቶ ከመከላከል ውጪ ሌላ አማራጭ የሌለው። ለአማራው ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር የሚባሉት እሱን የማይመለከቱ የድሎት ጥያቄዎች ናቸው። እነዚህ የመኖር ዋስትናው ለተረጋገጠ ህዝብ ህሊና የሚቀርቡ ጥያቄዎች ናቸው። የአማራው ህዝብ ለዚያ የታደለ ህዝብ አይደለም።

ወያኔ ሀርነት ትግራይ የተባለው የዘረኛ ፋሺሽት ድርጂት በተነሳበት ህዝባዊ ተቃውሞ ወደነበረበት የመመለስ ጎዳናው ወስጥ ለመግባቱ በቅርቡ ባደረገው የድርጂቱ ስብሰባ ላይ በገሀድ ታውጇል። ድርጂቱ ከገባበት አጣብቂኝ ውስጥ ለመውጣት የመረጠው ጎዳና በአማራው ላይ ካደረሰው የዘር ማጥፋት፣ ሀገሪቱ ላይ ካደረሰው ጥፋትና ዘረፋ ወንጀል አንጻር የወሰደው የአክራሪነት አቋሙ የሚጠበቅ ነው። ድርጂቱ ከተፈጠረ ጊዜ ጀምሮ ይዞት የመጣው የጸረ ኢትይጵያና የጸረ አማራ ካርዱ በተነሳው ሀገር አቀፍ ትግል ብትንትኑ በመውጣቱ በድርጂቱ ውስጥ ሳያጠፋው የማይመለስ ስብራት ደርሶበታል። ህወሀት ውስጠ መበታተን እንደደረሰበት ይፋ ያደረገ ስብሰባውን የዘጋው ሲመሰረት የድካሙ መለያ የሆነውን አውራጃዊነትን እንደገና እንዲቀበል መገደዱ ነው ። ታጥቦ ጭቃ እንደማለት።

# የትግሬ ወያኔ ወደ እውነተኛ ቁመናው ሲመለስ!

ይህ ወያኔ ተመልሶ ውደ ትንሽነቱ የወረደበት የፖለቲካ ውድቀት የታወጀበት ስብሰባ ያበሰረው ሌላው ነገር በትግሬ መህበረሰብ ውስጥ በጸረ አማራ ዙሪያ የነበር መሰባሰብን እንዳፈረሰው ሁሉ በኢትዮጵያ አቀፍ የገነቡትም የጸረ እትዮጵያና የጸረ አማራ ግንባር ወደመፈራረሱ ሂደት ውስጥ የመግባቱን ነው። የኢህዴግ የመፈራረስ ሂደት። ዛሬ በኢህዴግ ውስጥ ወያኔን የመናቅና የመፈታተን ሁኔታዎች መከሰት ከህወሀት የቁመና መሽብሸብ ዘንድ የመጣ ነው። ይህ ክስተት ድርጅቱ ጧት የተነሳለትን የትግራይ ሀገር የመመስረት አቅድ ከማፍረሱም አልፎ ኢሃዴግን ለዚህ ግቡ በታዛዥነት እንዲያገለግለው ሊመራው በሚያስችለው ቁመናው ላይ አይደለም። ይህ በድርጅቱ ውስጥ የተነሳውና ወደፊት በግልጽ የምናየው ድርጂታዊ መከፋፈል ወጥ አመራር አልባ አድርጎታል። ጧት የፈሩት የውስጥ ሽኩቻና ግጭት ውስጥ የመግባታቸው እድል ከፍት ሁኗል።

የዚህ ድክመት መዘዝ ዛሬ ድርጂቱ ሊወስዳቸው ወደተገደደበት የትግሬ-ኤርትራ (የትግራይ ትግርኝ) አዲስ ግኙኝነት ይወስደናል። የትግራይ ትግርኝ እንቅስቃሴን እንደገና የማንሰራራትት አባዜ። የኤርትራ-ኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ የወያኔ ሀርነት ትግራይና የሸአብያ የበላይነት ማንነት መፋታጊያ መገለጫ ነብር ማለት ይቻላል። ባከባቢው ያለውን ፖለቲካ ሀማሴን ይምራው አደዋ የሚለው ጥያቄ ማጠንጠኛው ነብር። ዛሬ የትግራይ ትግርኝን ፖለቲካ ማን ይምራው የሚለው በባድሜ ይዞታ ሲገለጥ የቆየ ነው። ዛሬ ወያኔ ከደረሰበት የህዝብ ምት ከውስጥ የተፈረካከሰና ወደ አውርጃዊ ፖለቲካው በመግባቱ ተዳክሟል። ይህ ሁኔታ በአንጻራዊነቱ ተደላድሎ በስልጣን ለተቀመጠ ሸአብያ መልካም ዜና ነው። ድርድሩን እሱ ይመራዋል። ለወያኔ የቀረ አማራጭ ሁለተኛ ደረጃ ቦታውን ይዞ፣ ባድሜንም አስረክቦ፣ ሌላም የሚከፈል የፖለቲካ ክፍያን ተቀብሎ ሊደራደር መገደዱ አይቀሬ መሆኑን መገንዘብ ነው።
ይሕ አዲሱ ትውልደ - ኤርትራነት ያለው የአደዋ አውራጃ ስብስብ አመራር ባለው አፍቃሪ ኤርትራና አክራሪ ጸረ ኢትዮጵያ አቋሙ ምክንያት የሚያደርገው የፖለቲካ እርምጃ በትግሬ ማህበረሰብ ውስጥ ሊፈጥር የሚችለውን ሽኩቻ ከወዲሁ መገመት ይቻላል። ዛሬም ገና ከጧቱ የተቃውሞ ድምጾች እየተሰሙ ነው። እድገታቸውን የምናየው ይሆናል። ለማጠቃለል ማለት የሚቻለው ህወሀት ወደመፈራረሻ ጎዳናው መግባቱን አስረግጦ መናገር የምንችልበት ጊዜ ውስጥ ገብተናል። የወደፊቱ የትግሬ ማህበረሰብ ከኢትዮጵያ ጋር የመቆየቱ ጉዳይ ውሳኔውን የሚያገኘው ከትግሬ ህዝብ እጅ ወጥቶ በሸአብያና በአደዋ አውራጃ ፖለቲከኞች እጅ መግባቱንም በሂደት እያየነው ነው።

በአማራው ህዝብ ትግል ዙሪያ የመጠናከር ሂደቱ እንዳለ ሁኖ በህወሀት መበተንና በአክራሪ የአደዋ ልጆች የሚመራ አዲስ አመራር መፈጠር ምክንያት በአማራው ህዝብ ላይ የሚወርደው እልቂት የመረረ ይሆናል። ትግሉም ወደ መደምደሚያው የሚወስደን ጎዳና ወስጥ በመግባቱ ለአማራው ህዝብ አስቸጋሪ ያደርገዋል።

ዛሬ በየትምህርት ቤቶች ደጃፍ ላይ የሚወድቅው የአማራ ወጣት እንደ ወላጆቹ እሱም ያለምንም የህግ ጥላ ከለላ ብቻውን በመቆሙ ነው። ዛሬ ወያኔ ትግሬ በነዚህ ያማራ ልጆችና ከመሀል ሀገር በመጡ የኢትዮጵያ ወጣቶች ላይ በትግሬ ክ/ሀግር በመፈጸም ላይ

# የትግሬ ወያኔ ወደ እውነተኛ ቁመናው ሲመለስ!

ያለው በዘር ላይ የተመሰረተ እልቂት ነግ በእጥፍ የሚመለስ ይሆናል። የአማራ ህልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጂት ይህንን እልቂት ያወግዛል። ከታጋዮ የአማራና የመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጎን በመቆም የወያኔ ትግሬን የአመጽ ክንድ ለማጠፍ ይታገላል። የወያኔ ትግሬ ዛሬ በማፈግፈግ ላይ ባለበት ጊዜ ከሚያደርስብን እልቂት ነግ በሽሽት ጎዳናው ውስጥ ሲገባ ከዛሬው የመረረ በትሩን እንደሚሰነዝር እንጠብቃለን። በመሆኑም ጊዜ ከአማራው ህዝብ ጋር አይደለም። ይህንን ተገንዝበን ለበለጠ እራስን የመከላከል ተግባር ህዝቡን የማዘጋጀት ስራ ሊሰራ ይገባል። ጊዜውን መተንበይ የሚያስቸግር ሁኔታ ውስጥ የገባንበት ወቅት ነው። የአማራው ህዝብ በየቀበሌው ተደራጅቶ እራሱን ከሚሰነዘርበት ጥቃት እንዲከላከል ታጥቆ እንዲቆም ማድረግ አስቸኳይ ስራችን ሊሆን ይገባል። መሀሉ ዳር ሲሆን ህወሀት ሲያፈገፍግ የነበረውን እንዳልነበር አድርጎ መሄዱ ለሱ የስትራተጂ ጉዳይ ነው። በዚያን ወቅት የሁሉ ጠላት እንደሆነ ሲሰበክና ሲሳደድ የኖረ አማራ እጣፈንታው የመጨረሻ አይሆንም ማለት አይቻልም። ይህ እንዳይሆን ለማድረግ ዛሬ ይህንን ህዝብ ማደራጀትና ማስታጠቅ ለይደር የምንይዘው ጉዳይ አይሆንም። ይህንን አድርገን የአማራውን ህዝብ ከእልቂት ስንታደግ ብቻ ነው የኢትዮጵያን አንድነት ማብሰር የምንችል።

ዛሬ በኢትዮጵያ ዙሪያ ያለ የሀይል አሰላለፍ በፍጥነት በመቀያየር ላይ ያለ ሂደት ነው። በመሆኑም ዘላቂ ወዳጅም ሆነ ዘላቂ ጥላት የምንለው የለም። የራስን ጥቅም ለማስጠበቅ ተለዋዋጭ አካሄድን የመከተልን አስፈላጊነት እንደመመሪያችን ልንይዝ ይገባል ። ግቡ ከተያያዝነው ትግል ውስጥ አሸናፊ ሁኖ መውጣት ነው። ትግሉ ረጅም፣ ግቡም እሩቅ፣ የመጨረሻ የአማራው ህዝብ ቁመናና ጥንካሬ፣ የሀገራችን ውርድና ቁመና ሊቀየር እንደሚችል ተገንዝበን ትግሉን ልንያያዘው ይገባል። ድርጂት ሀይልን የማባዛት ተግባር ነው። አማራው ይህንን እንደ አደረጃጀት ስልቱ ሊጠቀምበት ይገባል። በዙሪያው የአማራን ህዝብ እልቂት የሚቃወሙና ለእትዮጵያ አንድነት የሚታገሉ ሀይሎችን ማሰባሰብን እንደዋና እስተራተጂክ ግቡ አድርጎ ሊሰራ ይገባል። ብቻውን እራሱንም ለማደን ሀገሩንም ከመበታተን ለማትረፍ እንደማይችል መገንዘብ ይኖርበታል። የሱ ተግባር ለዚህ ዓላማ የቆሙ ሀይሎች እንዲሰባሰቡ መስራት፣ ማስተባበርና የጋራ አመራር የሚመሰረትበን መንገድ ማሳየት ነው። ለዚህ ተግባር ከተባበርን እናሸንፋለን።

ኢትዮጵያ በጀግኖች ልጆቿ ህብረት ከወደቀችበት ትነሳለች!

ውድ እናት ሀገር እትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!